የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ዘጠንኛ ዓመት ቁጥር 26 ሠመራ ሚያዚያ 4 ቀን 1998 ዓ.ም	በአፋርብሔራዊክልላዊመንግስት ምክርቤትጠባቂነት	9 Year No. 26 Samara ---- January .2005

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ..... ጽ 1

አዋጅ ቁጥር 26/1998 ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ

ቁጠባንና ኢንቨስትመንት ለማሳደግ ታክስ ከመክፈል ለመሸሽ ወይም በህጉ ውስጥ የሚታየውን ክፍተት ተጠቅሞ ታክሱን ላለመክፈል የሚደረገው ጥረት የሚያስከትለው ጉዳት ለመቀነስ የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን እና በጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርትና በመንግስት ገቢ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል የተጨማሪ እሴት ታክስ ስራ ላይ እንዲውል የተወሰነ በመሆኑ፣

የተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደር አመችነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለታክስ የሚመዘገቡ ሰዎች የሚከፈልበት አመታዊ ግብይት ከብር 500000 /አምስት መቶ ሺህ/ በላይ እንዲሆን የተወሰነ ስለሆነ፣

በንግድ ግንኙነት ፍትሃዊነትን ለማስፈን ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች ግዴታቸውን እንዲወጡ እና የታክሱ ስርዓቱ ሽፋን የተሟላ ለማድረግ የማስተካከያ ተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 47(3) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 26/1998 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ **2**

የተርን ኦቨር ታክስ

አዋጅ ቁጥር **308/95** ተፈፃሚነት

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 3 ከተመለከቱት በስተቀር የፌዴራል ተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/95 በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተፈፃሚነት ይኖረዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ተፈፃሚነት የሚኖረው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 97 በተደነገገው መሠረት የክልሎች ስልጣን በሆኑና የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሚመለከቱ ጉዳዮች ብቻ ይሆናል።

አንቀጽ **3**

በፌዴራል ተርን ኦቨር ታክስ ላይ የተደረጉ ለውጦች

1. በፌዴራል ተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/95 የተቀመጠው

   ሀ/ አንቀጽ 2(ሀ) በሚከተለው ተተክቷል

   2(10) እና የታክስ ባለስልጣን ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ የግብር ሰብሳቢ አካላት ናቸው።

   ለ/ አንቀጽ 2(13) በሚከተለው ተተክቷል

   «ሚንስቴር» እና «ሚኒስትር» እንደ ቅደም ተከተላቸው የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ እና የፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ እና የፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ናቸው።

   ሐ/ አንቀጽ 7(3) በሚከተለውተተክቷል፦

   በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩት ከታክስ ነፃ የመሆን መብቶች የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተተባበሪያ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

አንቀጽ **4**

የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ከሚያዝያ 1/1995 ዓ.ም በፊት ያልተከፈለው የሽያጭ ታክስ በሽያጭ እና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚሰበሰብ ይሆናል፣

አንቀጽ **5**

ይህ አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አቶ አስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

ጥር 1998 ዓ.ም

ሠመራ፣